# ቀጣሪዎች:
# እንዴት የበለጠ ከCOVID ደህንነቱ የተጠበቀ
# የሥራ ሁኔታ
# መፍጠር
# እንደሚቻል



በሥራቦታ የ COVID-19 ተገላጭነትን ለመቀነስ ቀጣሪዎች ኃላፊነት አለባቸው። ንግዶች ሰራተኞቻቸውን እና ደንበኞቻቸውን ከ COVID-19 ለመጠበቅ ከፍተኛ ሚና አላቸው።

## አንድሠራተኛ COVID-19 እንዳለበት ከተረጋገጠ ወይም ተጠርጣሪ ከሆነ መደረግ ያለበት

.

- ሰራተኛው ምርመራ እንዲያደርግ እና እንደ COVID አይነት ምልክቶች ካላቸው ከቤት እንዲቆዩ ያበረታቱ።
- ህጉ ቀጣሪዎች ለ COVID-19 አዎንታዊ ምርመራ ካደረጉ ወይም ቫይረሱ ካለበት ሰው ጋር ከተጋለጡ የተጠራቀመ የህመም እረፍት ወይም የእረፍት ጊዜ እንዲጠቀሙ ይፈቅድላቸዋል።
- ሰራተኞችን ወዳለዉ የድጋፍ ምንጭ ያመልክቱ www.kingcounty.gov/depts/health/covid-19/workers.aspx (በኢንግሊዘኛ ብቻ)

ማንኛውም ቀጣሪ በጤንነት እና ደህንነት ላይ ስጋት ስለደረሰበት በሠራተኛ ላይ ከሥራ ማባረር ወይም የበቀል እርምጃ መውሰድ በሕግ የተከለከለ ነው።

## ደህንነቱ የተጠበቀ የእረፍት ቦታዎችን እንዴት መፍጠር እንደሚቻል

ሠራተኞች በሥራ ላይ ዘና ለማለት የሚሄዱበት ቦታ COVID-19 ን ለማስተላለፍ ከፍተኛ ተጋላጭነት ያለው ቦታ ሊሆን ይችላል።ቀጣሪዎች በእረፍት ጊዜ ሠራተኞችን ደህንነት ለመጠበቅ አስፈላጊ እርምጃዎችን ሊወስዱ ይችላሉ።

- **የእረፍት ቦታዎች**: ቦታ ካለ ፣ ሠራተኞችን ውጭ ሁነው ዕረፍት እንዲያደርጉ ያበረታቱ፣ ወይም ሠራተኞች በደንብ ነፋሻ የሆኑ ተጨማሪ ክፍሎች ውስጥ ዕረፍት እንዲያደርጉ ይፍቀዱላቸው።
- **አቅም**: የእረፍት ክፍል ዉስጥ የሰዉ ብዛትን ከ50 ፐርሰንት ባልበለጠ ይገድቡ።
- **የእረፍት ሰዓቶች**: የሰራተኞችን መሰብሰብ ለመቀነስ የእረፍት ጊዜያትን ያሰበጣጥሩ።
- **የማህበራዊ ርቀት**: ሠራተኞች ሁሌም በእረፍታቸው ግዜ ጭምር ቢያንስ ከሌሎች 6 ጫማ ርቀት መጠበቅ አለባቸው። ሰራተኞች ሲቀመጡ ቢያንስ 6 ጫማ ተራርቀዉ እንድሆን ጠረጴዛዎችን እና ወንበሮችን አረርቀዉ ያስቀምጡ(የበለጠ ቦታ የተሻለ ነው)።
- **የአየር ማናፈሻ**: በቫይረሱ በአየር የሚተላለፈውን ስርጭት ለመቀነስ፣ HVAC ባለሙያ ጋር በመመካከር በሥራ ቦታ አየር ማናፈሻ ለማሻሻል የሚረዱ እርምጃዎችን (በኢንግሊዘኛ ብቻ) ለመውሰድ ያስቡ።
- **የፊት ሽፋን መጠቀም**: ሠራተኞች በማይበሉበት ወይም በማይጠጡበት ጊዜ የፊት ሽፋን እንዲለብሱ ያስታውሷቸው።
- **ምልክቶች**: የፊት መሸፈኛ እንዲለብሱ፣ የማህበራዊ ርቀት እንዲጠብቁ፣ እጅ መታጠብን እብዲያዘወትሩ፣ እና የግል ጤናቸዉን እንድቆጣጠሩ የሚያስታውሱ ምልክቶች ያስቀምጡ።

**ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ ሁኔታን ለመፍጠር ለሚገኙ የድጋፍ ምንጮች, KINGCOUNTY.GOV/COVID/BUSINESS-TOOLKIT ይመልከቱ (በእንግሊዘኛብቻ)**

January 12, 2021

Public Health
Seattle & King County